# ዳግም የአመፅ ጥሪ

በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ዛሬ የደረስንበት ወቅት ዳግም የአመፅ ጥሪ ለሕዝብ መተላለፉን የግድ የሚል ሆኗል፡፡ አንዳንዶችማ የዕብሪት ዕብሪት ሆኖባቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ--ከእኛ በቀር--የአመፅ ልምድና ችሎታ የለውም ብለው መሳለቅ ጀምረዋል፡፡ ጦርነት እንሰራባችኋለን ያሉን ዛሬ አቀራረብ ቀየር ቢያደርጉም መልዕክታቸው ግን ያው መሆኑ ደግሞ እየታየ ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት የወያኔ ቡድን የስልጣን ዕድሜውን ለማራዘምና መለስ ዜናዊ ሲፎክር እንዳለው ለ 50 ዓመታት ተጨማሪ ለመግዛት ዝግጅቱን እያጧጧፈ ነው፡፡ አንድም በሚቆጣጠረው የምርጫ ቦርድ አማካኝነት መጪውን ምርጫ አጭበርብሮ ለማሸነፍ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ሁኔታዎች ግድ ካሉ የወያኔውን የተጠላ ቁንጮ ቀይሮና በሌሎች ተክቶ የወያኔን ጠባብ የበላይነት ማስቀጠል የሚል ነው፡፡ ይህን ሂደት ለማጀብ ደግሞ ወያኔ የራሱን ካድሬዎች አዘጋጅቶ ለማስኬድ ከመጣሩ ሌላ ራሳችን ተቃዋሚ የሚሉ ወዶ ገባዎችና ተለጣፊዎችንም ለማሰለፍ ዕቅዱን በስራ ለማዋል ጀምሯል፡፡ በዚህም በዚያም ግን የወያኔን አገዛዝ መለስን ይዞ ሆነ ሳይሆን የሚቀጥልበትን መንገድ የሚፈልጉ በአንድ በኩል ሲሰለፉ በሌላ በኩል ደግሞ የወያኔን መወገድ የሚፈልጉ ሀቀኛ ሀገር ወዳድ ድርጅቶችና የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ተሰልፈዋል፡፡ ይህ የማይታረቅ ቅራኔ እንዴት ይፈታል የሚለው ዋና ጥያቄ ሲሆን የአፈታቱ ሁኔታ መሰረታዊ ለውጥ ይምጣ አይምጣን ወሳኝ ነው፡፡

ሕዝብ ፍላጎቱ የወያኔን አገዛዝ ማረቅና ማረም፤ማቀፍና ማፅናናት ሳይሆን አሽብሮና አስጨንቆ፤ወግቶና አንበርክኮ ማስወገድ ነውና ከአመፅ ሌላ ምንም መፍትሄ የለውም፡፡ የወያኔ ስርዓት የሚድን ሳይሆን መፈራረስ ያለበት ነው፡፡ ይህ አገዛዝ በታሪካችን ከተከሰቱ ስርዓቶች ሁሉ የከፋ፤መርዘኛና ፀረ ኢትዮጵያም ነውና ርዝራዡም በሀገራችን የማይገኝበትን ሁኔታ መፍጠር መቻል አለብን፡፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ ሕዝብ ማመፅ አለበት፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለ አመፅ ብዙ አስተማሪ ጠያቂ አይደለም፡፡ ዘመናዊ ስልቶችን በተመለከተ ሁሌም ልንማረውና ልናውቀው የሚገባ ብዙ ቢኖርም ሕዝብ መሸፈትና ማመፅ አስፈላጊ በሆነበት የሀይል ሚዛን ማጋደል ሳያግድው ለሀገሬ ለወገኔ ብሎ ተነስቶ ታግሏል፤መስዋዕትነትም ከፍሏል፡፡ አፄና ደጃዝማች ይህን ያንን ሰሩ ቢባልም አሸናፊውና ተዋጊው፤ ደም ገባሪው ሁሌም ሰፊው ሕዝብ ነበር/ነውም፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ትዕግስትና ቻይነቱ ጭቆናን እሽሩሩ ብሎ ለዘወትር ማቀፍን የሚጠቀልል አይደለም፡፡ ይህን ሀቅ ደግሞ አፄውም ቢሆኑ መንግስቱና ሙሶሊኒ በየፊናቸው ሊማሩት ተገደዋል፡፡

ማመፅ ማለት ወያኔን በምርጫ ቧልቱ ማገዝ  ማጀብ ማለት አይደለም፡፡ ማመፅ ማለት ከመለስተኛ ቁጣ እንኳን ርቆ ነጋ ጠባ ሕዝብን ከወሳኝ ትግል ለማራቅ መስበክ፤ ማውገዝ፤ መገዘት ሊሆንም አይጠበቅም፡፡ ማመፅ ስንል በጨዋነት ተብዬ ወይም የሰለጠነ ፖለቲካ ሽፋን ሽንፈትንና እጅ መስጠትን

በጨለምተኝነት አጅቦ ለሀገር ተምችም ለባዕዳንም ተውሳክ ተሸናፊ መሆን አይደለም። አመፅ ስንል ሕዝብ በሁለገብ ትግል አገዛዙ ለመደምሰስ ወይም ለማስወገድ የሚያካሂደውን ነው። በሰላም ትግል በስተጀርባ ተጠልለው ለአገዛዙ ማደርን ወይም መሞዳሞድን የሚሰብኩ ሀሳውያንና የበግ ለምድ የለበሱ ቀበሮዎች እንደሚሉት ሳይሆን ሕዝብ ከወያኔ አገዛዝ ጋር ያለው ቅራኔ የማይታረቅና መሰረታዊ ነው። የማይታረቅን ቅራኔ ለማቻቻል ብዙ ጊዜ ተሞክሮ በወያኔ እምቢተኛነት ውጤት አልባ ሆኗል። ለዕርቅና ሰላም ጉባዔ ሀገር የተመለሰውም አበራ የማነአብ እነሆ እስከዛሬ በእስር እየማቀቀ ነው። ጨዋ ፖለቲካ፤የሰላም ፖለቲካ በግንቦት 7 በወያኔ ፌዴራል ፖሊስ የቀብር ስነ ስርዓት ተድርጎለታል። አገዛዙ በጠመንጃ ሞክሩኝ መልዕክቱን የነሽብሬ ደሳለኝና የስንቱን ንፁህ ደም አፍሶ አስተላልፏል። ይህን በደም የተጨማለቀ ቡድን ወዳጅ ማለቱ ወይም በኢትዮጵያዊነት ፈርጆ ዳግም ከእሱ ለመደራደር ጎንበስ ጎንበስ ማለቱ ሀገርንም ወገንም አሳፋሪ መሆኑ ዛሬ ጥያቄ ሊያስነሳ ባልተገባ ነበር። የሚያሳዝነው ግን አሁንም ከወያኔ አገዛዝ ጋር ለመተቃቀፍ ሳቅ ሳቅ ማለት የጀመሩ ማፈሪያዎች መበርከታቸው ነው።

ሕዝባዊ አመፅ በከተማም በገጠርም የሚካሄድ ነው። ከሕዝብ አቀፍ ሰላማዊ ሰልፍና ተቃውሞ እስከ የቀበሌ ሰልፎችና ተቃውሞዎች፤ የስራ ማቆምና የሙት ከተማ አድማዎች፤ በአገዛዙ ተቋሞች ላይ ሻጥሮችና ማዕቀቦችን፤ ሞሎቶቭ ነዳጅ ጠርሙስ ውርወራዎችና ከዚያም በላይ ትጥቅ እንቅስቀሴን ሁሉ ያካትታል። በተደራጀ መልክም በግብታዊነትም ሊካሄድ ቢችልም መደራጀቱ ለተሻለ ውጤት የተመቸ ያደርገዋል። የአመፁ ኢላማ የአገዛዙ ዋና ዋና ተጠቃሚዎችና አራማጆች ሲሆኑ በአገዛዙ የአፈና ተቋሞችም ላይ እርምጃ መውሰድ አስፈላጊ ነው። ሰላዩ፤ አሾክሿኪውና ሰው በላው ካድሬውም ምሱን ማግኘቱ የግድ ነው--በተለይ ከሕዝብ ጎራ ተደባልቅ ጥሪን ጆሮ አልሰጥ ብሎ በወንጀሉ ከቀጠለ ። የአገዛዙ ዋና ዋና አጋሮችም የአመፁ ጅራፍ ሊጮህባቸው የሚገባቸው ናቸው። መሳሪያውም ገንዘቡም ከጠላት እጅ ያለ ነውና ይህን የሕዝብ ንብረት ማስከበሪያውን የተጠና መንገድ በስራ ማዋል ይቻላል። ዋናው ግን በሆነው መንገድ ለመታገል ስንነሳ በመጀመሪያ የአገዛዙ መውደቅ ላይ ሙሉ እምነት መኖሩ ወሳኝ ነው። አምፀን ወያኔን ወደ ጠረጴዛ ዙሪያ አምጥተን እንተቃቀፈው የሚሉትም ተሳስተዋል።አምፀን የወያኔን ቡድን ማውደም የሚል መሆን አለበት ዋናው አላማና ግብ።

ይህን ካመንበት ቀጣዩ ከባድ አይደለም። የተናቀው ሕዝብና ለዘመናት ትገዛታለህ የተባለው ሕዝብ በአመረረና ፀረ ወያኔ በሆነ አመፅ የእነ መለስን ቡድን ማርበድበድ አለበት። በጎራቸው ሽብር፤ ጭንቀትና ፍርሀት እንዲሰፍን ማድረግ ይገባዋል።ትግል ሳይግም ሳይፋፋም የምህረት ደወል ሊያቃጭል ሊሰማ አይገባም። ይወገዳል እንጂ ምንው አይወገድ በሚል መፈክርና እምነት ዙሪያ ተሰልፎና ታግሎ አገዛዙ ማንኮታኮት አስፈላጊ ነው። ሀገርን ለማዳን፤ አንድነትን ለመጠበቅ፤ የሕዝብን መብት ለማስከበር። ይህን ትግል የሚያደናቅፉትን ከወዲሁ ማጋለጥ፤መታገልና ማግለልም ተገቢ ነው። መሰል ከሀዲዎችናነ ባንዳዎችን ሰንደቅ ዓላመ ይዞ የሚቀበለው ሁሉ በጊዜ መታረም

ይኖርበታል። ታሪክ በመጥፎ እንዳይመዘግበው፤ከሕዝብ እንዳይጣላ። ማነው ሀቀኛ ሀገር ወዳድ? ማነው በሀቅ ፀረ ወያኔ? ለዚህ ትክክለኛው መልስ መሰጠት አለበት። ፀረ ትግሉንም፤ ከወያኔ ጋር በይፋም ሆነ በምስጢር ከመይ ቀኒሃ የሚባባለውንም ከሕዝብ ጎራ መንጥቆ ማውጣት ያስፈልጋል። ሕዝባዊ አመፅ በሕዝብ ጎራ ገብተው የወያኔን ስራ የሚሰሩትን መንጣሪና አስወጋጅ መሳሪያ ነው። ለዚህ ወሳኝ ትግል የማይጠቅሙ ድርጅቶችና ማህብራዊ ስብስቦች ለህልውናቸው ማጠየቂያው ህዝብን ለመታደግ የሚል ሊሆን አይችልም። ሲጦም ከመረቁም ከስጋውም ነው። ወይ ከህዝብ ጎን ወይም ከጠላቱ ጎን መሰለፍ ነው ያለው ምርጫው። በሀገር አድኑ ወሳኝ ሕዝባዊ አመፅ መሀል ሰፈራ ሀገር አሳጪ ቅንጦት ነው። ለነገሩማ ከሕዝብ ያልቆመ ከወያኔ አልቆምኩም ቢልስ በማለቆሙ ብቻ እርዳታው ለወያኔ አይደለምን?

ዳግም የአመፅ ጥሪ ያስተጋባል። ሕዝብም ጆር ሊሰጠው ይገባል። ለዕብሪተኞቹ የአመፅ ችሎታና ፅናታችንን፤ ማምረራችን በተግባር እናሳያቸው።